# የሕዝባዊና የኦሊጋርኪ ፍልሚያ በቀደምት ጊዜያት

በማርች 9,1861 አብሃም ሊንከን የአሜሪካውን የፕሬዝደንት ምርጫ እንዳሸነፉ ዩናይትድ ስቴትስ ወደ መበታተን ተቃርቦ ነበር፡፡ በምርጫው ማግስት ያሸናፊነታቸውን እወጃ ንግግር ባደርጉባት ደቂቃ፤የሚከተሉት ስቴቶች (ክልሎች)፤- አላባማ፤ሚሲሲፒ፤ ሳውዝ ካሮላይና፤ ጆረጂያ፤ ሉዊዚያናና፤ፍሎሪዳ ከፌዴራል ሥርዓቱ (ከኅብረቱ) ለመገንጠል ውሳኔ አስተላለፉ፤ የቴክሳሱም መሪ መገንጠልን ባለመደገፋቸው በመፈንቅለ መንግሥት ከሥልጣናቸው ተወገዱ፡፡

የቀድሞውም ፕሬዝደንት ጄምስ ቡካነንም ነባር ካቢኔ የሃገሪቱን ካዝና አሚጦ ከመሄዱም በላይ፤ የመከላከያ ሚ/ሩ ጆን ፍሎይድ ቀድም ብሎ ለታቀደ መፈንቅለ መንግሥት የአመጽ ኃይሎችን ለማስታጠቅ የጦሩን መሳሪያ ሀብትና ቁሳቁስ በሚስጥር ወደ ደቡብ አሸጋግሮ ነበር፡፡ በዚያም የሳውዝ ካሮላይና ጦር መምሪያ በዚሁ ሕገ-መንግሥቱን ለመናድ በተዘጋጀ ኃይል ከቦ የነበረ ሲሆንና፤ የሊንከን ነፍስ ግድያ እንዲሁም የምርጫ ውጤት ቆጠራን የማስተጓጎል እቅድም ተቀምሮ ነበር፡፡ ጄነራል ዊንድፊል ስኮት፣ የታወቁ የ1812 የጦር አርበኛና የወቅቱ የፀጥታ ኃላፊ፤ የታቀደውን የሴራ መረጃ አስቀድመው ይዘው ስለነበር ዋና ከተማዋን የፌዴራል የፀጥታ ኃይላቸውን በመመደብና ከባድ ማስጠንቀቂያ በመስጠት ሕገመንግሥታዊውን የምርጫ ቆጠራ ለማደናቀፍ የሚሞክርን ማንኛውንም ኃይል እንደሚደመስሱ በማያሻማ ቃል ግልጽ አደረገው አስቀመጡ፡

ይህ ፍጥጫ ለፕሬዝደንት ሊንከን የአገራቸው የውስጥ የሰሜንና የደቡብ ትግል ብቻ ሳይሆን ከእንግሊዙ ኢምፔሪያሊዝም ጋር የሚፋለመው የመላው የአለም ህዝቦች ፍልሚያ ነበር፡፡

ሊንከን የእንግሊዝ ዘውዳዊ ገዢዎች የአሜሪካንን (<u>ሰው ሁሉ በተፈጥሮው እኩል ነው</u>) የሚል አስተሳሰብ አምርረው መቃወማቸው ብሎም የዘውድ ህልውናቸውን የሚፈታተን ሆኖ እንደሚያዩት ያውቁ ነበር፡፡ ንጉሣኑ የአሜሪካንን ስቴቶች(ክልሎች) የመገነጣጠል አንቅስቃሴ ማስጠንሰስ፤ መፈንቅለ መንግሥት ለማካሄድ ሙከራ ማዘጋጀታቸውንም፣ የሳቸውንም ሕይወት ለማጥፋት ከመሞከርም እንደማይመለሱም ጠንቅቀው ተረድተውት ነበር፡፡

ቀድሞውንም በ1804 የመጀመሪያው የኢኮኖሚ ኃላፊና የብሔራዊ ግምዣ አዛዥ የነበሩትና፤ ስብእናን (የሕዝብን መብት) በቀዳሚነት ያስከበረውን የአዲሲቱ ዩናይትድ ስቴትስ ኢኮኖሚያዊ ፍልስፍና አፍላቂ የነበሩትን አሌክሳንደር ሃሚልተንን የነፍስ ግድያ ያካሄደባቸው ለነዚሁ ለእንግሊዞች ራሱን ያስገዛ ኤረን-በር የተባለ ሥርዓተ አልበኛ ነበር፡፡ ኤረን-በር በጊዜው የአዲሲቱ ዩኤስ ምክትል ፕሬዝደንትነት ሥልጣን የነበረው ሲሆን በወቅቱ ከለንደን በተደረገለት ድጋፍ እቅድና ንድፈ ሃሳብ ፤በወታደራዊ አመፅ ከሉዊዚያና በሜክሲኮ እስከ ፓሲፊክ ዳርቻ ድረስ ያለውን ምዕራባዊ ግዛት ለመገንጠል ሲል በወቅቱ የእንግሊዝ አምባሳደር በነበረው አንቶኒ ሜሪ የበላይ መሪነት ተንቀሳቅሿል፡፡ በ1812 ከ8 አመታትም በኋላም ኤረን-በር ለሚላላክለት የእንግሊዝ ዘውድ የገዛ ሃገሩ የአሜሪካን ዋና ከተማ ዋሺንግተን ዲሲን ዶግ አመድ አድርገው አወድመውታል፡፡ ብሎም የኒው ኢንግላንድ (አዲሲቱ እንግሊዝ) በሚል ስም ተደጋጋሚ የመገንጠል ሙከራዎችን ሞክረዋል፡፡

ሆኖም አሜሪካ የተደቀኑበትን ፈተናዎች በመቋቋም ብሎም በመቀልበስ ሕልውናውን በማረጋገጡ፤ የእንግሊዝ የስለላ መረብ የሚስጥር ኃላፊ በነበረውና “በብሪቲሽ ዌስት ኢንዲስ” የሽፋን የንግድ

ድርጅት ስም ሲንቀሳቀስ የነበረው ሎርድ ሼልበርን ሲያካሂድ የነበረውን ሴራ ለማቋረጥ ተገዷል፡፡ የሼልበርንን ሃላፊነት በቀጣይነት የተረከበው ሎርድ ፓልመርሰተን ዘይቤውን በመለውጥ ወደ የባሪያ ጉልበት የመጠቀም አሰራር በመግባት፤ የአሜሪካን የገንዘብና ምጣኔ ሀብት ሚዛን ለማዛባት ከተቻለም ለማፍረስ ተንቀሳቀሰ፡፡ ይህ የባሪያ ሥርዓት የአሜሪካንን የንግድ ሥርዓት ለማናጋትና የእንግሊዝን አለማቀፋዊ ኢምፔሪያሊዝም የበላይነትን ለማረጋገጥ የተመረጠ መንገድ ነበር፡፡ ይህ በነፃ የባሪያ ጉልበት ላይ የተመረኮዘው ሥርዓት ገበያ በአዳም ስሚዝ “የነፃ ገበያ ሥርዓት” (free trade)በመባል ተሰየመ ፤ ከምዕራብ አፍሪቃ በመነሳት በሮያል አፍሪካ፣ በብሪቲሽ ዌስት ኢንዲስና በመሳሰሉ ድርጅቶች እየታደኑ የተሰበሰቡ የአፍሪቃውያን ታጋቾች ጉልበት በነፃ የምርት መገልገያነት ግብአት በመሆን ተወሰደ፡፡ በዚያም ነፃ ጉልበት በግብርና የጥጥ ምርትን በብዛት ማምረት ቻሉ፡፡ ከሰብሉ 75 በመቶው ወደ ብሪታኒያ ይላክና የብሪታኒያ ላባደሮች በዝቅተኛ ክፍያ የተለያዩ የአልባሳት ውጤቶችን ያመርቱ ነበር፡፡ ከምርቱም ዝቅተኛ ጥራት ያለው የጨርቃጨርቅ ውጤት በጊዜው የግርማዊነቷ ተመራጭና ከፍተኛም የሕዝብ ቁጥር ወደነበረው ቅኝ ወደ ህንድ ይላክ ነበረ፡፡ የሕንድ ሠራተኞች ግን ለራሳቸው አልባሳትን ማምረት የማይፈቀድላቸው ስለነበረና ሁሉም ለእንግሊዝ ቅኝና የንግድ ትስስሩም ሰለባዎች ስለነበሩ፤ በውድ ዋጋ ያለምርጫቸው የሚረከቡትን ልብስም የኦፒየም ሰብል አርሶ በማቅረብ ከፍተኛ ዋጋን ለመክፈል ይገደዱ ነበር፡፡ የኦፒየሙ ምርት ለብዙሃኑ ቻይና ሕዝብ ይሸጥ የነበረና በሱስ የመቆጣጠሪያ መሣሪያነት የዋለ ነበር፡

ይህንንም ግንኙነት ላኪህ አዳም ስሚዝ በርካሽ ገዝቶ በውድ መሸጥ (buying cheap & selling dear) በማለት የሰየመው ነው፡፡ ይህም የንግድ መረብ የዘውድ ሥርዓቱ የህልውና መሠረት ስለነበረ፣ ትስስሩ በየትኛውም ክፍል ቢስተጓጎል ሁለመናው እንደሚስተጓጎል በመገንዘብ ደህንነቱን በታላቅ ትጋት መጠበቅን አጠናከሩ፡፡

ከሥርዓቱ ወጥመድ ያመለጠውን አዲሱን አሜሪካን ሎርድ ፓልመርስተን “ከእንደ ዩናይትድ ስቴትስ ያለ ጋጠወጥና ዋልጌ ሕዝብ ጋር መደራደር አያስፈልግም፣የባህር ኃይል ስለሌላቸው የወደብ ከተሞቻቸውን በሙሉ በቅጽበት በማቃጠል ትምህርት እንሰጣቸዋለን” ብለው በትዕቢት የደነፉት ያኔ ነበር፡፡ ፓልመርስተን በወቅቱ የአሜሪካንን መፍረስ ተስፋ ያደረጉ ስለነበረ የኮንፌደሬት ጎጠኞችን ሲረዱና ሲያጠናክሩ ነው የኖሩት፡፡ በጃንዋሪ 1/1861 ፓልመርስተን ለእንግሊዟ ንግሥት በፃፉት የደስታ መግለጫ ከፈረንሳይ ጋር በመተባበር ብሪታኒያ ስላደረገችው የቻይና ቤጂንግን ወረሮ በቁጥጥር ሥር ማዋል፤ በአሜሪካም የመፈራረስ ምልክቶች ስለሚታዩ መልካም ተመሳሳይ አጋጣሚ እንደተመቻቸ ገልጿል፡፡

ሊነከን በ1861 ተመረጡ፤

እንግሊዝ በሩሲያ ላይ በ1854 ዘመተች፤

ቻይና የኦፒየምን ምርት ወደ ወደቧ ከመራገፍ ለመከልከል ስትሞክር በ1859 በእንግሊዝ ተመታች፡፡

አብራሃም ሊንከን በጊዜው አሜሪካ ላይ ጦርነት አይቀሬ መሆኑን ያውቁም ያስቡም ነበር፤ ይህም፣ በአንድ ወገን ዘመናዊው ሕዝባዊ የአሜሪካ ሥርዓት መርህና፣ በተቃራኒው ደግሞ ጨቋኙና ኋላቀሩ እንግሊዝ-መር የጥቂቶች የዘውድ አገዛዝ ሥርዓት የምዕራቡን ዓለም ለመውረስ ወሳኝ ትግል ሆነ፡፡ ቆራጡ ሊንከን ወደ ሥልጣን ሲመጡ፤ አለማቀፋዊ ሕዝባዊነትን በመምራት ከእንግሊዝ ዘውዳዊ

ሥርዓት ጋራ መፋለምን መርጠው ለመሥዋእትነትም የተዘጋጁ ታጋይ መሆናቸውን በግልጽ ከመናገርም በላይ፣ ውለው አድረውም በተግባርም ሰማዕት ሆነዋል፡፡

የሊንከን መርህ(All men are created equal)"ሰው ሁሉ እኩል መፈጠሩን ነው"፣ ለሳቸው ሕገ መንግሥቱና የነፃዋ የአሜሪካ ሉአላዊነት የትግላቸው ህልውና ዋና ምሰሶዎች ነበሩ፣ በንግግራቸውም ላይ 'የሃገራችን ነፃነትና ሉአላዊነት ከእንግሊዝ ጭቆናዊ አገዛዝ መላቀቅ ብቻ ሳይሆን ትግላችን የሰው ልጆችን ስብዕና የሚያስከብርና ለመላው ዓለምም ሕዝቦች በቀጣይ ፋናወጊም ስለሆነም ነው'፡ ከላይ የተጠቀሱትን የሕዝቦች ፍላጎት ሳናሳካ ከምንቀር በዚህች ቦታ መሞትን መርጣለሁ ሲሉ ቃል ኪዳን ፈጸሙ፡፡

ትግሉም በአሜሪካ ድልን ከተጎናጸፈ በኋላ በቀጣይ ወደ አውሮፓ እንደሚሻገር ሊንከን ብቻ ሳይሆኑ እንግሊዞቹም በሚገባ ተረድተው ነበር፣ ስለዚያም ነበር በታላቁ መሪ ላይ የሕይወት ማጥፋት ሙከራ በተደጋጋሚ ያስሞከረባቸው፡፡ ቆይቶም ሊንከን ይህን በማጠናከር ላይ ሆነው ነበር የወደቁት፣ ሆኖም የሳቸው መሥዋዕትነት ትግሉን የበለጠ በቁጭትና በቁርጠኝነት እንዲቀጣጠል ረዳው፡፡

ሊንከን በእንግሊዝ ድብቅ እጅ በተላከው የኮንፌዴሬት ጦር ላይ ድል በተቀዳጁ በ5ኛው የቀን ነበር ጆን ዊልትስ ቡስ ተኩሶ የገደላቸው፡፡ ገዳያቸው የፓልመርትሰን ቀጥረኞች ከነበሩ ከነ ጆን ሳንደርስ ና ፣ጆን ሰራት በተመሳሰይ የሚስጥር የእንግሊዝ ተቋማት ከተሠማሩ ወንጀሎኞች ስምንቱ በእስር አራቱ በስቅላት የሞት ፍርድ ሲፈረድባቸው፣ ከላይ የተጠቀሱቱ ግን ወደ ብሪታኒያ በመሸሽ የተደላደለ ኑሮዋቸውን ቀጥለዋል፡ ሊንከን ቢሰዉም ሕዳሴያዊ አስተምሯቸው አገሪቱ ወደ ፈጣን የእድገት ጎዳና እንድትገባ መሠረትም ምክንያት ሆናት፡፡

የሊንከን ተከታይና የትግሉ ቀጣይ መሪም የሆኑት ጆን ኩዊንሲ አዳምስ የተቀበሉትን ኃላፊነትና በሠማዕታቱን ጅምር የትግል መስመር በመቀጠል አሜሪካንን ከጫፍ ጫፍ ለማልማትና የህዝቦችን መብት በበላይነት ማረጋገጥ ጀመሩ፡ ብሎም ከሕዝቦች ጫንቃ ላይ የዘውድ አምባገነናዊ ሥርዓትን ለማስወገድ በትጋት ቀጠሉ፡፡ ሥርዓታችንና ርዕዮታችን እያደረ የሚያድግና በዱላ ቅብብሎሽ በመጨረሻ የሚያሸንፍ ይሆናልም አሉ፡፡

የአሜሪካ እድገት በዋናነት ራሱን ከእንግሊዙ የነፃ ገበያ በተፃራሪ በማስኬዱ፣በርካሽ የሰው ጉልበት የተመረቱ የእንግሊዝ ምርቶችን ማስገባት በመከልከልና  መሠረተ ልማትን በብዛት በመገንባት ምናልባት ከዛሬዋ ኢትዮጵያ በቀር በታሪክ ተወዳዳሪ ያልተገኘለትን እድገትና ውጤታማነት አስመዘገበ፡፡

በሊንከን ካቢኔ የኢኮኖሚ ጉዳይ አማካሪ የነበሩት ሄንሪ ሲ.ኬሪ እንዳስቀመጡት *'በታሪክ የእንግሊዝ ነፃ ገበያ ሥርዓትን የሞከሩ ሁሉ ሕዝባቸውን፣የምግብ አቅርቦታቸውን፣የተፈጥሮ ሃብታቸውን፣ ለም መሬታቸውንና፣ባጠቃላይ በጊዜው የደረሱበትን ሥልጣኔ በሙሉ አጥተቷል፤ ነፃ ገበያ በደረሰበት ሁሉ መጨረሻው ጥፋት ኋላቀርነትና ጦርነት ነው፡፡'*

መንግሥት የሕዝቡን ጥቅም ከውጭ ከሚመጣ የተደራጀ ፉክክር በመከላከሉ (protectionism) የአሜሪካ ኢኮኖሚ የብሪታኒያን በአጭር ጊዜ በልጦታል፡፡ ከሁለት አሥርት አመታት ባነሰ የሥራና የትግል ጉዞ በኋላም አማካሪው ሄንሪ ሲ.ኬሪ ከመላው ዓለም የፈጠራ ሁሉ የሳይንስና የፖለቲካ መሪዎችን በመጋበዝ የዩ.ኤስ.ኤ ኢኮኖሚያዊ መርህ ግብር ውጤትን አሳይተዋል፡፡

በዚህም የሰው ልጆችን የፈጠራ ችሎታ ከምንም ቁሳዊ ንብረት በላይ ዋጋ በመስጠት፣ የሰው ሀብት የሁሉም ዓይነት ሃብቶች ዋነኛ ምንጭ መሆኑን በግልጽ ለይቶ በማስቀመጥ በጥቅም ላይ ማዋል የሚል መርህ ነበር፡፡

እንግሊዞች የተፈጥሮ ሀብትን በዓለም ዙሪያ ለመቆጣጠር ሌት ከቀን ሲማትሩ፣ አሜሪካ በአንፃሩ ስብዕናን በማበረታታት ከጭቆናው ዓለም የሚመጡትን ስደተኞች የኑሮና የሥራ ዕድል በመስጠት ፍሬያማ ውጤትን አስመዝግቧል፡፡ አሜሪካ የባቡር ቴክኖሎጂን በማሳደግ ከአውሮፓ፣እሲያ ፣ሩሲያ፣ጋር ታላቅ ስኬታማ የንግድ ልውውጥ አስመዘገበች፡፡ አለምአቀፋን ጉልተኛውንና ጨቋኙን የዘውድ ሥርዓት ለመታገል የአሜሪካ ምሁሮች፣ የጦር ኃይል መሓንዲሶች፣ኢኮኖሚስቶችና ዲፕሎማቶች፣በቡድን በመሆን ይህንን የአሜሪካ ርዕዮተ ሃሳብ ወደ መላው ዓለም ፓሲፊክንና አትላንቲክ ውቂያኖሶችን በማሸጋገርና ወደ ላቲን አሜሪካም በመዝለቅ ማስተማርን ተያያዙት፡፡

በሩሲያ ይህ ቡድን ከመጓጓዣ ሚ/ሩ *ካውንት ሴርጌይ ቪታ፣ ዲሚትሪ ምንደሌየቭ* እና ከሌሎችም ጋር ሆነው የሳይቤሪያን አቋራጭ የባቡር ሐዲድ በሊንከኑን የአሜሪካ አገር አቋራጭ በምሳሌነት በመውሰድ ዘረጉ፣ የመጀመሪያውም ባቡር ፋርጎ በዩ.ኤስ ፊላዴልፊያ የተፈበረከው Baldwin ኩባንያ ነበረ፡፡ በ1890 የሩሲያ መሪዎች ቀጥተኛ የባሕር ላይ ድልድይ ከአሜሪካ ጋር ለማገናኘት አቅደው ነበር፡፡

በፈረንሣይም ተመሳሳይ የባቡር መስመር መረብ እድገት ቀጥሎ፣ የውጭ ጉዳይ ሚ/ሩ የናይልን አካባቢ በባቡር ለማያያዝ ሥራ ጀመሩ የኢትዮ ጂቡቲም መሥመር የዛው አካል ነበር፡፡

ጃፓን በተመሳሳይ ፈጣን የመጓጓዣ ልማት እድገት በማምጣት ከአሜሪካ ጋር ወዳጅነቷ አይሎ፤ የመጀመሪያውን የግል ባንክም በአህጉሩ ቆረቆረች፡፡

በቻይና ወደቦች ከእንግሊዝ እንደሚመጣው ኦፒየም ሳይሆን የአሜሪካ የሲቪል መሐንዲሶች የሠሯቸው ጭነቶች የባልድዊን ባቡሮችን ነበር የሚያራግፉት፤ የኬሪ ወዳጅ ሆርተን ባርተር የቴሌግራፍና የባቡር ግንባታዎችን በፋይናንስ ለማገዝ የመጀመሪየውን የቻይና-አሜሪካ ባንክ ከወቅቱ የቻይና መሪዎች ጋር ጀመሩ፡፡

በጀርመን በቻንስለር አውቶባን ቢዝማርክ አመራር አሜሪካዊው አስተሳሰብ ከሃገሩ ውጭ ከፍተኛውን ውጤት በማስተግበር ከሦስት አመታት ጥናት በኋላ በአዋጅ የበፊቱ የነፃው ገበያ ሥርዓት ተሽሮ በታሪፍ ሥርዓት ተተካ፡፡ ተከትሎም ጀርመን በዓለም መድረክ ጠንክራ ወጣች፡ ከፈረንሳይ ኢንዱስትሪያሊስቶችም ጋር በመተባበር ከሩሲያው የሳይቤሪያ ሐዲድ ጋር የራሳቸውን ለማገጣጠም ከበረሊን እስከ ባግዳድ ቀድሞ ያልነበረ መስመርም ለመዘርጋት መንቀሳቀስ ጀመሩ፡፡

በወቅቱ አብዛኞዎቹ የዓለም ወደቦችና የባህር ላይ (maritime based power)የአለምአቀፍ ንግድ በብሪታኒያ ቁጥጥር ሥር ስለነበረ ሃገራት በብሪታኒያ ሥር ካልሆነ መንቀሳቀስ አልቻሉም ነበር፡፡ በአንፃሩ አሜሪካ-መሩ የባቡር መስመር ልማት የየብስ ግንኙነቶችን በመፍጠር የእንግሊዝን የዓለም ንግድን የመቆጣጠርን የበላይነት አቅም ስላሚያምነው ይህን ለማስቆም እንግሊዝ መላው አለምን በጦርነት ለማበጣበጥ ማሴርና መንቀሳቀስ ጀመረች፡፡

የእንግሊዝን ጂኦፖለቲካዊ እቅድ የጀርመኑ ቢዝማርክ ተረድቶ ስለነበረ የፈረንሳይ፣ ሩሲያንና ብሪታኒያ እኩይ ጥምረትና አጋርነት ጦር ቢመጣ ጀርመንን በመክበብ በቀላል ለማጥፋት

እንደሚያስችላቸው በመጠርጠር ከተጠቀሱት ሃገራት ባሻገርም ከኦስትሪያ ንጉሣዊ ቤተሰቦች ጋር ወዳጅነትን መሠረቱ፡ በሚሥጥርም ከሩሲያው ንጉሥም ስምምነትን አደረጉ፡፡

በቦልቲክስ የሃይማኖት ጦርነትን በኦርቶዶክስና በሌላው የክርስትና እምነት ተከታይ መካከል ለመጀመር የተዘጋጀን የእንግሊዝ ውጥን ቢዝማርክ ቀድሞ በፈጠረው የኦስትሪያና ሩሲያ ወዳጅነት ለማምከን ችሎ ነበር፡፡ ቢዝማርክ የእንግሊዝን ስውር አካባቢን የማተራመስ አላማ ጠንቅቆ በመረዳቱና እየቀደመም በመራመዱ የእንግሊዝ ዋነኛ አላማዋ ይህን መሪ ማስወገድ ሆነ፡፡

ልዑል ኤድዋርድ አልበርት የሎርድ ፓልመርትሰን የተንኮል ደቀመዝሙርና የንግሥት ቪክቶሪያ ልጅ ራሱን፣ የብሪታኒያ የውጭ ጉዳይ ቀማሪ በማድረግ ለሚቀጥሉት ሃያ ዓመታት የተወጠነውን የእርስ በርስ ትርምስ ለማሳካት የጀርመኑን ቢዝማርክን ለማስወገድ ሥራ ጀመረ፡፡ ኤድዋርድ አልበርት ራሱ እንደተናገረው “ዋነኛው ኃይል የየብስና የባህር ላይ የጦር አቅማችን ሳይሆን የሰዎችን የውስጥ ግላዊ ድክመት በመለየት ለራስ አጀንዳ ማካሄጃ መጠቀሚያ ማድረግ መቻል ተወዳዳሪ የሌለው ከባድ መሣሪያ ነው”፡፡ በዚያም ረገድ ነበር፣ በጊዜው በየአገሩ ንጉሣኑ እርስ በርስ የተጋቡና ሁሉም ከእንግሊዟ ንግሥት ፍልፍሎች ስለነበሩ፣ የጀርመኑም ንጉሥ በ1890 ቢዝማርክን ከቻንስለርነት ጡረታ እንዲያስወጣው ተደረገ፡፡ ይህ ነበር የአሜሪካ ጥንስሱን አስተሳሰብ ለመቀልበስ ኢምፔሪያሊስቶች የወሰዱት የመጀመሪያ እርምጃ፣

ከዚያም ቢዝማርክ በጥበብ ያገቱትን የፈረንሳይ የሩሲያና የብሪታኒያ ኅብረት በማጠናከርና በሁሉም የአሜሪካ መር አስተሳሰብን የተቀበሉ የላቲን አሜሪካ አውሮፓና እሲያ ሃገራት ላይ የጥፋት ቀስት ተነጣጠረ፡፡ በ1894 የፈረንሳ ፕሬዝደንት ሳሪ ካርኖት ተገደሉ፣ በሐሰት ውንጀላም የፈረንሳዩ የጦር አዛዥ (የአይሁድና ጀርመን ዝርያ የነበራቸው) ጀነራል ድራይፈስን የሞት ፍርድ አስፈረዱባቸው፡ ይህም ለቀጣይ 12 ዓመታት ያህል ፀረ-ይሁዲና ፀረ-ጀርመን አስተሳሰቦችን በፈረንሳይ እንዲስፋፉ ትልቅ ተዋጽኦ ፈጠሩ፡፡ የእንግሊዙ ኤድዋርድ አልበርት ለቢጫ ሕዝቦች ያለውን ጥላቻ በመደበቅ ወደ ጃፓን በመመላለስ በጀርመን ቪለሃምን እንዳታለለው የጃፓኑንም ንጉሥ ሚጂ ለማሳመን “እንግሊዝ አውሮፓን እንደምትመራው ጃፓንም እሲያን መምራት ይገባታል፣ ለዚህም ደግሞ የእንግሊዝ አጋርነት ሁሌም ካጠገባችሁ ስላለ በቀላሉ ይሳካል፡”

በዚያም መበረታታት በ1894 ጃፓን በብሪታኒያ በተመረቱ የባህር የጦር መሣሪያ ኃይል ቻይናን በመውረር የሩሲያና የአሜሪካ ኢንዱስትሪያሊስቶች ሐዲድ ሊዘረጉበት ያቀዱበትን ድንበር ተቆጣጠረች፡፡

የተቀረው አለም በግጭቶች ሲታመስ አሜሪካ ሰላሟንና ልዕልናዋን ጠብቃ እድገትና ልማቷን ገፋችበት፡፡ በሊንከን በ1860 ዓም ተጀምሮ ለ30 ዓመታት እስከ ፕሬዝደንት ዊሊየም መክኬንሊ 1900 ዓም የተካሄደው ትግል ብዙ ውጤቶችን አስመዝግቧል፡፡ ፕሬዝደንት ዊሊየም መክኬንሊም በንግግራቸው “30 የራስን ጥቅም ከውጭ ኃይላት የመከላከል አካሄድ (protectionism) በእርሻ፣በማዕድን ልማትና በኢንዱስትሪ በአለም የመሪነትን ስፍራ አስጨብጦናል፡ ዩናይትድ ኪንግደም (እንግሊዝ) ከኛ በፊት ክፍለ ዘመናትን ቢያስቆጥርም ጥለነው ሄደናል፡፡ ባለፉት 50 በላይ ዓመታት እንግሊዝ በነፃ ገበያ መርሃ ዘዴ እንደ ዴሞክራቶቹ ሲንቀሳቀስ ነበረ፣ እኛ (ሪፓብሊካን) በ31 ዓመታት ብዝሀነትን ያማከለ ጥቅምን የማስከበር አመራር ተከትለን፣ በማንኛውም መስፈርት ወይም ሚዛን መላው ዓለምን ቀድመናል፡፡ ጠንካራው የመንግሥት አመራር (protectionism/strong developmental) ከማንኛውም ፍልስፍና በተሻለ ተመራጭነቱ አያጠያይቅም፡፡

በ1896 የመክኬንሊ አመራር ስላስደነገጣቸው እንግሊዞች ከምርጫ ዋዜማ ጀምሮ ሂደቱን ለማስቀልበስ ተላላኪዎቻቸውን አሰማርተው ተንቀሳቀሱ፡፡ በቀደሙት መሪዎች (ኩዊንሲ አዳምስ) ታቅዶ የነበረውን የመላው አውሮፓ-ሩሲያ (በድልድይ)-አሜሪካና እስከ ደቡብ ጫፍ ላቲን-አሜሪካ የባቡር ሐዲድ መረብ ተዘርግቶ ቢያልቅ፤ከምዕራብ አውሮፓ እስከ ደቡብ የአኅጉሩ መጨረሻ ጫፍ ያለ መርከብ መመላለስ ሊቻል ሆነ፡፡ ይህም ለእንግሊዙ ሥርዓት መበለጥ አመላካች ሊሆን ነበር፡፡

ነገር ግን የፕሬዝደንት መክኬንሊ ምክትል በድንገት ከዚህ ዓለም ስለተለዩ፣ቴዲ ሩዝፌልት (የነፃ ገበያው አቀንቃኝ የእንግሊዝን የዘውድ የአንድን ዘር ከሌላው የማበላለጥ ሥርዓት ናፋቂ) በቦታቸው ተተኩ፣የእንግሊዝ የባንኮች የጥምረትን ሙሉ ድጋፍም ተቸራቸው፣

ቴዲ ሁለት በአርአያነት የሚከተሏቸው ሰዎች ነበሯቸው፤-

1ኛ. አጎታቸው ጄምስ ደን ዊሊያም ቡለክ፤ በጦርነቱ ወቅት ለእንግሊዝ የስለላ ድርጅት አመራር ሆነው ያገለገሉና የአሜሪካንን ብዙ መርከቦች በፈንጂ ያሰጠሙ በአሜሪካ የወንጀል ተፈላጊ ሲሆኑ፣

2ኛ. ሃገር ከዳተኛው አልፍሬድ ቴነ ሜሃን፡ የአሜሪካንና የእንግሊዝ አዲስ ትስስር መጀመር ይፈልግ ነበር፤

ፕሬዝደንት መክኬንሊ በድጋሚ ሲመረጡም ምክትላቸው የእንግሊዙን ሥርዓት ናፋቂና ተስፈኛ ሲሆኑ በሊንከን አስተምሮት የተጀመረውን የመሠረተ ልማትና የባቡር መሥመር ዝርጋት በፍጥነት ማስቀጠልን ገፉበት፡፡ ሁለተኛውን የአመራር ዘመናቸውን በጀመሩ በ6ወራቸው በፓን አሜሪካን ኮንፈረንስ የ50ሺ ተሰብሳቢዎች ቀልብ የወሰደ በመሠረተ ልማት ግንባታ ላይ ያተኮረ ንግግር አድርጉ፣ ታዳሚውም በጋለ ስሜት አዎንታዊ ድጋፉን ገለጸላቸው፡፡ በነጋታው መክኬንሊ በጥይት ተመተው ወደቁ ሠማዕትም ሆኑ፣ ገዳዮቹም የፈረንሳዩን መሪ ከ7 ዓመታት በፊት የገደሉትና በለንደን በተማከለው የሽብርተኝነት መረብ የተሰማሩ ወንጀለኞች ነበሩ፡፡

የቴዲ ሩዝቬልት ፕሬዝደንትነት ወሳኝነቱ፣ የተጀመረው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ ከልማታዊ አቅጣጫው ወደ የጥቂቶች ንጉሣዊያኑ ኪራይ ሰብሳቢ ሥርዓተ መስተዳድር መቀልበሱ ነው፡፡

የመክኬንሊ መውደቅ በአንቱ የሰለጠነውን ቴዲን የበላይ የኃላፊነት ኮርቻ ላይ አፈናጠጠው፣ ሥልጣንም ከሕዝባዊው የነሊንከን ልማታዊ አመራር ወደ እንግሊዝ-መሩና ፀረሕዝቡ  የነፃ ገበያ (ኪራይ ሰብሳቢ) አስተሳሰብ ባንድ አፍታ ተገለበጠ፡፡ ይህ የአሜሪካ አቅጣጫ መቀየር የእንግሊዙ ዘውድ በአሜሪካም ሆነ በመላው ዓለም ወደር የለሽ ፈላጭ ቆራጭ አደረገው፡፡

በ1904 በእንግሊዝ ገዥዎች ተጽዕኖ የፈረንሳዩ አመራር ከእንግሊዝ ጋር የጦር ትብብር ፈረመ፣ በ1902 የጃፓኑም ንጉሥ ተመሳሳይ ውል ገቡ፣ ጃፓን ከሩሲያ ብትዋጋ እንግሊዝ የአውሮፓ ኃይላትን ከሩሲያ ረድፍ እንዳይሰለፉ ልታደርግ ቃል ገባች፣ ስለዚህም ጃፓን የሩሲያ አርተር ወደብን በድንገት በመምታት፣ ከ37 ዓመታት በኋላ የአሜሪካ ፐርል ሃርበር እንደደገመችው አደረገች፡፡ ጃፓን ለጦርነት ሙሉውን የብድርና የጦር መሣሪያ ድጋፍ የተቀበለችው ከእንግሊዝ ነበር፡፡

በ1905 ጃፓን ሩሲያን እንዳንኮታኮተቻት፣ የአሜሪካው ቴዲ ሁለቱን ወገኖች የሰላም ስምምነት አፈራረሟቸው፡፡ ወዲያውም ብሪታኒያ በመቀጠል የሩሲያውን ዛር (ንጉሥ) ለመጣል በሩሲያ አብዮትን አስቀሰቀሱ፡ በጊዜው የሩሲያ መሪዎች እነ ሰርጌ ቪታ የነበራቸው መላው ዓለምን በባቡር

የማስተሳሰር ህልም በጦርነት አስከፊ እውነታ ተተካ፡፡ ከፍልሚያውም በኋላ እንግሊዝም የበላይነቱን ጨበጠች፣ የጃፓኑንም ንጉስ እንደ እንግሊዝ የነገሥታት ቤተሰብ የክብር ማዕረግ ተሸለመ፡፡

በ1905 የሩሲያው አፄ (ዛር) ኒኮላና የጀርመኑ አፄ (ካይዘር) ዊልያም በድብቅ ተገናኝተው ለትብብር ተስማሙ፤ በ1907 ግን የሩሲያው ኒኮላ ቃላቸውን በማጠፍ ከእንግሊዝ ጋር በመስማማት ፈረንሳይን በመጨመር ሦስተኛው ተባባሪ በመሆን ጀርመን ላይ ለማበር ተስማሙ፡፡ ቢዝማርክ በጡረታ ከመወገዳቸው በፊት በጥበብ አቻችለው ያቆዩት የአካባቢው ፖለቲካ የትስስር ሚዛን ተዛባ፡፡

በዚያን ሰዓት የእንግሊዙ አፄ (ካይዘር) ኤድዋርድስ ከአሜሪካው ቴዲ ጋር የሞቀ የወዳጅነት ግንኙነት ነበረው፣በየክፍለ አለማቱ የሁሉም የእንግሊዝኛ ቋንቋ ተናጋሪ መሪዎች አውስትራሊያ ድረስ ተመሳሳይ ፍላጎት እንዳላቸውም ይነጋገሩ ነበር፡፡ ፕሬዝደንት ትዲ የመክኬንሊን የባቡር ዝርጋታ ፕሮጀክት በመሰረዝ፣ ሠፋፊ መሬቶችን በተፈጥሮ እንክብካቤ ስም የሊንከን አስተምሮት የነበረውን የአዳዲስ ሠፋሪ አልሚዎችን ወደ ልማት መግባት አገዷቸው፡፡ አሜሪካ የእንግሊዙ ሥርዓት የስጋት ምንጭነት ከመሆን ወደ ቀዳሚ አጋርነት ተለወጠ፡ የመጨረሻው የሃይማኖት ጦርነት በቦልኪንስ ተጀመረ፡፡

ብሪታኒያ ልዩነቶች ባሉበት ሁሉ፤ለምሳሌ በእምነት የፕሮቴስታንት፣ ኦርቶዶክስ ወይም የኦቶማኑ የሙስሊም ሃይማኖት ተከታዮች ባሉበት በተፈለገው ደቂቃ መበጣበጥን ማስጀመር እንደሚችሉ ተረድተው ነበር፡፡

በጁን 1914 የኦስትሪያ ሃንጋሪያው ዘውድ ወራሽ ልዑል ዱክ ፈርዲናንድ በቦዝኒያ ሳሪዬቮ በመኪና ሲጓዙ በስርዓተ አልበኞች ጥይት ተመተው ሞቱ፣ ኦስትሪያም በአጸፋው ሰርቢያ ላይ ጦር አወጁ፣ አፄ (ዛር) ኒኮላ በሰርቢያ ወገን ጦርነቱን ተቀላቀሉ፣ በተመሳሳይመ ጀርመን ፈረንሳይና እንግሊዝም በሌላው ወገን ገቡበት፡፡ የመጀመሪያው የዓለም ጦርነት እንግሊዝ እንደወጠነው ተጀመረ፣ የአመራር ብቃት ባልነበራቸው መንግሥታትና በእንግሊዝ የተንኮል ሴራ ትርምሱ በስኬት ተጀመረ፡፡ ትርጉም ያልነበረው የ4 ዓመቱ ያላቋረጠ ጦርነት ሠለጠንን ያሉትን የአውሮፓውያንን ኤኮኖሚና ኃይል ካሚጠጠ በኋላ ያለአሸናፊ ተደምድሟል፡ ውጤቱም የሞራል ኪሣራና የእንግሊዝ እቅድ መተግበር ብቻ ነበር፡፡

በ1915 ፕሬዝደንት ውድሮው ዊልሰን አሜሪካንን በእንግሊዝ ንጉሠ መንግስት ረድፍ በማሰለፍ ወደጦርነት ቀላቀለ፣ አክራሪ የኬኬኬ (የነጭ አሪያን ዘር የበላይነት ቡድን) ደጋፊ የነበረው ዊልሰን ምርጫ ለማሸነፍ የበቃው ሦስተኛ ቡል ሙስ የተሰኘ ተወዳዳሪ ፓርቲ በቴዲ ሩዝቬልት በመደራጀቱና፤ በሥልጣን ላይ በነበሩት ተመሳሳይ የኮንፌደሬት ሃሳብ ተከታይነት ስሜት ያላቸው የብሪታኒያ አጀንዳ አራማጆች በመኖራቸው፤ በነሱ ባይሆን ኖሮ ምናልባት አሜሪካ ወደ ጦርነቱ አትቀላቀልም ነበር፡፡

ለ24 ዓመታት በዳግማዊ አፄ ኤድዋርድስ የታቀደው፣የተጠነሰሰውና የተተገበረው የአንደኛው የዓለም ጦርነት ሴራ የብሪታኒያን የዘውድ አገዛዝን የማስወገድ ሕልም ከመሠረቱ አጠፋው፣ በአውሮፓና በእሲያ በሊኒከን ዘመን የአሜሪካን ርዕዮትን የተቀበሉ አገራት እርስ በራሳቸውን እንዲጠፉፉ ነበር የተዳረጉት፡፡ በአሜሪካም ዊልሰን ከብሪታኒያ ጋር በመጣመር የሊንከንን አስተሳሰቦችን ነቅሰው

አስወገዱ፡ የብሪታኒያ ገዢዎችም ከመቼውም የበለጡ ጠንክረው ወጡ፣ የሊንከን አስተምሮት መልሶም እንዳያንሰራራ እስከወዲያኛው የሉዐላዊ ብሔራዊ መንግሥታትን መደራጀትን ከሕጎች መፋቅ ጀመሩ፡፡

ይህም የሞተው የቀዳማዊው ኤድዋርድስ ሃሳብ አገራትን በማያቋርጥ የእርስ በርስ ጦርነት አቅጣጫ የማስኬድና ደካማ እንዲሆኑ ማድረግ ሲሆን፣ በተተኪው የ1ኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የብሪታኒያ የስለላና ደህንነት ኃላፊ በነበረው በኤች ጂ ዌልስ ተጠናክሮ ቀጠለ፡፡ ዌልስና ግብራበሮቹ ወዲያውኑ በዓለም ዙሪያ ሁሉ የቅራኔዎችን የዘር ጥንስስ በየሃገራት ውስጥና በሃገራት መካከል ያኖሩ ጀመር፡፡ ይህ አካሄድ ደግሞ በመጨረሻ ብሪታኒያ ከሥሯ የዓለም ሃገራትን በሙሉ በመቆጣጠርና ማስተዳደር አዲሱን የዓለም ዋህድ መስተዳድር መጀመር (ዘ ኒው ወርልድ ኦርደር) ነው፡፡

ለዚህም የመጀመሪያው ማሳያ የብሪታኒያ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በ1919 የጠቅላላውን የጦርነቱን ኪሣራ በጀርመን ላይ በመፍረድ የቢዝማርክን ቀደም የስኬት ውጤትን መበዝበዝና ብሎም የጀርመንን ሉዐላዊነት ማፍረስ ነበር፣ በከፍተኛ ምርታማነታቸው ቀዳሚ የነበሩትን የግብርና መሬትና የተፈጥሮ ሀብት ወረሱ፣ መርከቦች፣ባቡሮችና የምርት መገልገያዎች ግማሹ በካዝና የነበረ ወርቅም በይፋ ተዘረፈ፣ ህዝባዊ ድጎማዎች ተሰረዙ፣ኢንዱስትሪዎች ወደግል ይዞታነት ተሸጋገሩ፣ የዶች ማርክ ውድቀትን ጠቋሚ ተከታታይ የፕሮፓጋንዳ ዘመቻ በማካሄድ በ1923 የዋጋ ግሽፈቱ ከቁጥጥር በመውጣቱ በተጨባጭ ለንደን ጀርመንን መልሳ በኢኮኖሚ ተቆጣጠረች፡፡

በተመሳሳይም በደቡብ ምዕራብ እሲያ በሚስጥር ስምምነት ፈረንሳይና የብሪታኒያ-አረብ ቢሮ የሳይስፒኮ ውሉታን በመፈራረም፣ ለብሪታኒያ ግዛት ፍልስጤም የትራነስ-ጆርዳንና ኢራቅን ሲያደርጉ ለፈረንሳይ ደግሞ ሊባኖስና ሶሪያ ሸለሙ፡ እስከዛሬዋ ድረስ የሚከሰቱት የዘርና የሃይማኖት ግጭቶች መጀመሪያው ይህ የሃያላኑ የክፋት እርሾ ዘር መሆኑ ሊሠመርበት የገባል፡፡

የጀርመኑን ሥርዓት ከውስጡ ያፈረሱት ባንኮችና የገንዘብ ተቋማት ራሳቸውን በአሜሪካም በቁልፍ ቦታዎች ላይ አመቻችተው ለማኖር ተዘጋጁ፡ ጄ.ፒ.ሞርጋን ባንክ በዎል ስትሪት የብሪታኒያው በአሜሪካ የገንዘብ ክንድ ሆኖ ተቋቋመ፣ ከ1860ዎቹ ጀምሮ ብሪታኒያ ስትሞክር የነበረው ድብቅ ኢኮኖሚን የመቆጣጠር ጥረት ተሳክቶ በ1920ዎቹ የሞርጋን ሃውስ በሁሉም የአሜሪካ ፋይናንስ መረቡን ዘረጋ፡፡ በመንግስት ሕዝብና በግል ሥራዎች ላይ የበላይ አበዳሪ በመሆን ተቆጣጠረው፡፡ ጄፒ ሞርጋን አሜሪካ ታላቁ ኃይል በመሆን በበላይነት ካሰማራው የብሪታኒያ የዘውድ ቁንጮ በስተቀር በአለም ተወዳዳሪ የለሽ ሆነ፡፡ ይህ ግዙፍ የገንዘብ ተቋም የለንደንና የዎልስትሪት ተሿሚ ፕሬዝደንቶች በመሰይም ነበር የአሜሪካ መዋቅርን ማፍረስ የተቻለው፡

በ1928 ጆን ጄ.ራሰኮብ (የ ጄ.ፒ.ሞርጋን ታዛዥና በሚስጥራዊ የውስጥ ግብይይት የኪራይ ስብሰባ ሃብት ያካበተ) በወቅቱ በኪሣራ ላይ በነበረው ዴሞክራቲክ ፓርቲ ውስጥ ከፍተኛ አመራርነትን ያገኘ ሲሆን 300 ሺህ ዶላር ለፓርቲው በመለገስ ከእዳ ነፃ አረጋቸው፡፡

በሪፓብሊካኑ ፓርቲ ደግሞ የኢምፔሪያል ጃፓንና የጣሊያኑ ፋሽስት ሙሶሊኒ የገንዘብና ሀብት ባለሥልጣን የነበረና የጄ.ፒ.ሞርጋኑ ቶማስ ለማንት ሆነ፡፡

በ1925 ይኸው ቶማስ ለማንት የሙሶሊኒ ፓርቲ በተቸገረበት ወቅት ከጄፒሞረጋን 100 ሚሊዮን ዶላር ነበር የለገሰው፡ ቅጹም የፕሬዝደንት ሀርቨር ሁቨርንም የየዕለት አማካሪም ነበረ፡፡

በ1929-1933 ጥቁር አርብ (black Friday) በመባል የሚታወቀው የገንዘብ ውድቀትና የዋጋ ንረት ሥርዓቱን አናጋው፣የኢንዱስትሪና የእርሻ ግንኙነት ብቻ ሳይሆን ጠቅላላ የሕብረተሰቡ መዋቅር በመፍረሱ ሰፊ ሥራ አጥነትና ተስፋ መቁረጥ ነገሠ፡፡ ይህ ሰዓት ነበር በ1936 ሞርጋን በፈረንሳይ የፋሽስት መንግሥት ለማሰየም የሞከረው፣ በስፔንም አብዮት የፍራንኮ የፋሺስት መንግሥት ሥልጣን የያዘው፣ ሂትለር በሥልጣን ነበር፣ ሙሶሊኒ በሥልጣን ነበር፣በብሪታኒያ የፋሺስት ደጋፊ እንቅስቃሴ አይሎ ሴኔተር ራንድ ሎረድ ቢቨርብሩክ ለመሾም ቀርበው ነበር፣ እነዚህን ክስተቶች የሚደግፉ ባንኮች በዎልስትሪት ነበሩ፣ ከደጋፊዎቹም አንደኛው የፕሬዝደንት ጆረጅ ቡሽ አያት ፕሬስካት ቡሽ ነበሩ፡፡ በጋሪማን ኢንተረስት የገንዘብ ተቋም ሥር ፕሬስካት ቡሽ  ለሂትለርን ገንዘብ ያስተላልፉ ነበር በሃገሩ ውስጥ ደግሞ በራይክ ባንክ ፕሬዝደንት ያልማር ሻክ ሚሊዮኖች ወደ ናዚ ፓርቲ የተላለፍ ነበር፡፡

በ1923 የጀርመን ፕሬዝደንት ሂንደርበርግ ሂትለርን በቻንስለርነት እንዲሰይም ተገደደ፣ አንድ ወር ሳይሞላውም የራይትስኮት ህንፃ ላይ በናዚ ሰዎች ፍንዳታ ተደረገ፣ ናዚዎች ኮሙኒስቶችን በሐሰት ለመወንጀልና ፍርሃትን በሕዝቡ ላይ ለማድረግ ተጠቀሙበት፡፡ በዚህም ምክኒያት ሂትለር የአስቸኳይ ጊዜ አምባገነን ሥልጣን አገኘ፡፡

በአሜሪካ ሥራ-አጥነት 25% ደርሶ፣ ኪሣራና የኢኮኖሚ ውድቀት ስላየለ በወቅቱ ስለአለምአቀፍ ሁኔታዎች ግድም የሚሰጠው ሰው አልነበረም፡፡ የሕዝቡ ትኩረት በቀጣዩ ምርጫ ከጊዜው ችግር የሚያወጣቸውን የሚፈልጉበት ጊዜ ነበር፡፡ በዴሞክራቲክ ፓርቲ ውስጠ ደንብ ላሸናፊነት 2/3ኛ ድምጽ ያስፈልግ ነበር፣ ጆን.ጂ.ራስኮብ መሪነትን ለማረጋገጥ መንቀሳቀስ ሲጀመር ብቸኛውና አስጊ ተፎካካሪው ፈራንክሊን ዲ.ሩዝቬልት ነበር፣ ስለዚህም የተፎካካሪዎችን ቁጥር በማበራከት ማንኛውም ሌላ ተፎካካሪ እንዲያሸንፍ ጥረቱን ተያያዙት፡፡ የሩዝቬልት የምረጡኝ የንግግ መድረኮች ላይ ቦዘኔዎችን በቅጥር በማሰማራት ሰላምን ለማወክ በተደጋጋሚ ሞክረዋል፣ የሚዲያ ዘመቻም በማካሄድ፣በ1ኛ፣2ኛ፣3ኛ ዙር ሩዝቬልት እንዲሸነፉ አድርገዋል፣ ቀጥሎም ለሩዝቬልት ደጋፊዎች በሙሉ አስገራሚ ቴሌግራም መጣ፣ ይህም “የፓርቲያችንን ጥንካሬ ለመጠበቅ የኦሃዮውን ኒውተን ቤከር መምረጥ ይሻለናል” የሚል ነበር፡፡ ሩዝቬልትም በበነጋው በአጸፋው “ትግላችን የአላማ ነውና እንገፋበታለን፣ የፓርቲያችንን የብዙሃን ፍላጎት በጥቂት የዎልስትሪት ባለሃብቶች መቀየር አንፈቅድም” በማለት አረጋጉት፣ በምርጫውም አሸነፉ፡፡

ለሩዝቬልት ይህ ትግልም የድሞክራቶች የውስጥ ትግል ሳይሆን ከልጅነቱ ጀምሮ ጠንቅቆ የተረዳው የእንግሊዝ ኢምፔሪያሊዝም ከሊንከናዊው የሕዝብ ፍላጎት ጋር የሚያደርገው ትንቅንቅ ነበር፡፡ የፍራንክሊን ሩዝቬልት ቅም አያት አይዛክ ሩዝቬልት የመጀመሪያው የገንዘብ ሚኒስቴር የነበሩትና የተገደሉት የሃሚልተን የቅርብ ወዳጅ ነበሩ፣

በ1920 ሩዝቬልት በ38 ዓመት እድሜያቸው የዴሞክራቲክ ፓርቲ ም/ፕሬዝደንት  ሆነው ተመረጡ፣ በከሊንከን መርህን ተመሳሳይነት ያለው አቅጣጫ ይዘውም ሥራ ጀመሩ፣ ይህም የተፈጥሮ ሃብትን ማልማትና የሕዝቦችን ኑሮ ማሻሻል ነበር፡፡ በዚህ ጊዜ ነበር ፖልዮ በሽታ የያዛቸው፣ የአካል ጉዳተኛ በመሆንና ከእንቅስቃሴዎች ስለተገቱት የአልጋ ቁራኛ ሆነው በጥልቅ ማንበብና መመራመር ጀመሩ፡፡ ይህ አጋጣሚ የሰው ልጅ ዋነኛ ማንነቱ አእምሮው መሆኑን ማሳያ ሊባል ይችላል፡፡ ፍራንክሊን ሩዝቬልት ታመው ስለተቀመጡ የአስተሳሰባቸውን አድማስ የማስፋት ሥራ በሰፊው ተያያዙት፣ የሥነሕይወት ግንዛቤያቸውንም አዳበሩ፡፡

ቀጥሎም በ1928 ለኒው-ዮርክ መስተዳድርነት ተወዳደሩ፣ በንግግራቸውም ብሔራዊው መንግሥት የሕዝብ እንጂ የኮርፖሬሽኖች ፍላጎት ታዛዥ መሆን እንደማይገባው ተናገሩ፣ ተመረጡም፡፡ ሥራቸውንም ሲጀምሩ ይህንኑ ማስፈጸም ጀመሩ፡ ለሕዝብ ሴፍቲ ኔት፣ የውሃ መብራትና ኃይል ግብይይትን በትኩረት መቆጣጠርን ጀመሩ፤ በ1929 ሩዝቬልት በይፋ የዴሞክራቲክ ፓርቲ የሊንከንን መርህ መቀበልና የራሱ እንዲያደርገው ወሰኑ፡፡ የነሊንከን የነበረው ሪፓብሊካን ፓርቲ መነሻው የነበረውን ሕዝባዊነት መስመር ፈጽሞ ትቶ ወደ ኪራይ ሰብሳቢ የባንኮች፣የገንዘብ ተቋማትና የትልልቅ ባለሃብቶች ጥቅም ጠባቂነት አስተሳሰብ ተቀየረ፡፡ የኒው ዮርክ ስኬታማ የመስተዳድራቸው የሥራ አፈጻጸም የሚቀጥለው የዴሞክራቶች በፌዴራል የፕሬዝደንት እጩነት ተመራጭ እንዲሆኑ ቢያዘጋጃቸውም፣ ባለ ብዙ ሃብቱ ራስኮብ ሊቀናቀናቸው ብዙ ጥረል፣ ብሎም ዴሞክራቲክ ፓርቲ እንዳያሸንፍና የበላይ ሥልጣን በፍራንክሊን ሩዝቬልት እንዳይያዝ ከውስጥ ታግሏዋል፡፡

በ1932 በዴሞክራቲክ ፓርቲ የውስጥ ፉክክር፣ በይፋ የፋሺስት/ናዚ አራማጆች ሥልጣኑ በሕዝባዊ አስተሳሰብ አራማጁ ሩዝቬልት ከሚያዝ ፓረቲውን በሁለት ለመክፈል ሞክረዋል፡፡ ፓርቲውን መክፈል ስላልሆነላቸው እነሱ የበላይነትን እንዲያገኙ ተንቀሳቀሱ፡፡ በአንጻሩ የሩዝቬልት እርምጃ ሃሳቦች በየብዙኃሃኑ የነቃ ተሳትፎ እንዲወሰኑ በማድረግ በሕዝባዊ መዋቅሮችና ማኅበራት የውይይት መድረኮችን ፈጥረው ሕዝቡን አደራጁ፡፡ በሠራዊት ግንባታ መልክ ሕዝብን በሰፊ በማንቀሳቀስ የጥቂት ጥገኛ ባለሃብቶችንና በታሪክ ኦሊጋርኪ ተብሎው የሚታወቁትን የጥቂቶች የመደብ የበላይነትን ማምከንና በብዙኃኑ ትብብር ማሸነፍ ችሏል፡፡ የሕዝቡን ከ80% በላይ ድምጽ ለማግኘት ያስቻለው የፍትሐዊነትና ሰብእናን የማስከር ብሎም አገሪቱን ቀድሞ ከተሸነፈውና በእጅ እዙር ሁለቱንም ተፎካካሪ ፓርቲዎች ሊቆጣጠር የተቃረበውን የእንግሊዙን የነፃ ገበያ (ጥገኛ) የአናሳዎችን ደባ ድል መቷል፡፡

በ1933 ምርጫ እንዳሸነፉ የነፍስ ግድያ ተቃጥቶባቸው ተረፉ፣ ይህም የተለመደው የለንደን ሙከራ መሆኑን በንግግራቸው አስረግጠው ዘግበውታል፡፡ ሽብርተኝነትን መፍራት የለብንም፣ ጥገኞትና ኪራይ ሰብሳቢዎች በሕዝብ ድምጽ ተወግደዋል ብለው በትክክል አስቀመጡት፡፡

ከሊንከን ጀምሮ እንደሩዝቬልት ይህንን የትግል መስመር የተረዳ መሪ አልነበረም፡፡ ፍራንክሊን ሩዝቬልት ታላላቅ የኢኮኖሚ ፖሊሲ ለውጦችን ቀይሰው ወዲያው መተግበር ጀመሩ፣ ከነዚውም መካከል ዋነኛው የዋና ረዳታቸው ሂሪ ሆፕኪንስ እርምጃዎችን ማየት ይበቃል፤ ሂሪ በሥራ ገበታቸው በተመደቡ በመጀመሪያዎቹ ሦስት ሰዓታት፡ በስልክ ብቻ 11 ሚሊዮን ዜጎችን በመቅጠር ወደ ሥራ በማስገባት፣ 20 ሚሊዮን ዶላር ወጪ በማድረግ፣በሲቪል መልሶ ማቋቋም፣በገጠር የመብራት ኃይል አቅርቦትና የመስመር ዝርጋታ ተቋምና፣ የአራቱ ማዕዘን ፕሮጀክት የተባለውን መሠረቱ፡፡ ይህም በዓለም ታሪክ ተወዳዳሪ ያልነበረውን የሰላም ጊዜ የሕዝብ እንቅስቃሴ ሆኖ ተመዝግቧል፡፡ ለምሳሌ የ"ቴኔሲ ሸለቆ ባለሥልጣን" በተባለ ተቋም ኋላ ቀር የነበረን አካባቢ በክልሉ በሚፈሱ የቺን ወንዞች ላይ 33 ግድቦችን በመገንባት ጠፍ የነበረውን መሬት በማልማት፣ ለገበሬው ስልጠናን በመስጠት የውኃ ሃብታቸውን እንዲቆጣጠሩና እንዲያስተዳድሩ፣ የተራቆተውን አፈር መልሶ እንዲያገግም ሊያረጉና በመስኖም በመጠቀም ምርታማነትን እንዲያሻሽሉ፣ የኃይድሮ ኤሌትሪክም ተጠቃሚ እንዲሆኑ ብሎም በከተሞች ኢንዱስትሪ መልሰው እንዲያገግሙ በማድረግ፣ ከሁሉም በላይ የሰው ልጅ ችግሮች በራሱ በሰው ምክኒያታዊነት በሳይንስና በትምህርት እንደሚሸነፉ ለማሳየት አስችሎታል፡፡ የመልሶ ማቋቋም ኮሮፖሬሽኑን እንደገንዘብ ተቋም በመጠቀም የሃገሪቱን የገንዘብ መበደር አቅምን ለማሳደግ ቻሉ፣ የተገኘውንም የገንዘብ አቅም

በግብአትነት በመጠቀም ትምህርት ቤቶችን፣ ቤተመጻሕፍትን፣የአየር ማረፊያዎችን፣ ፖስታ አገልግሎትን አስፋፉ፡፡ የወርቅ ዋጋ ግዥፈትን ተቆጣጠሩ ብሎም በዎልስትሪት የገንዘብ ለዋጮች የዋጋ ተማኝና የጥቂት የግል ባለሃብቶች የነበረው ሥርዓት ላይ ዘመቱ፡፡

የብሪታኒያው (ኦሊጋርኪያዊ) ሥርዓትና የዎልስትሪት አጋሮቹ በጄ.ፒ.ሞርጋኑ ራሰኮብ መሪነት በሰፊ የሚዲያና የስም ማጥፋት ዘመቻና 500,000 ሰዎችን በማደራጀት መንግሥትን በኃይል ለመቆጣጠር ተንቀሳቀሱ፣ ይህም እቅድ በጀርምን ሂትለርን በመጠቀም እንዳደረጉት ከነባር የመከላከያ አመራር ውስጥ ተቀባይነት የሚኖረውን መኮንን በመምረጥ በመሪነት ነውጥ ለማካሄድ የነድፉት አቅጣጫ ነበር፡፡ ጡረተኛው ጀኔራል ስሜድሊ በትለርን ነበር የመረጡት፣ ሆኖም ጀኔራል ስሜድሊ እውነተኛ አሜሪካዊና ያለፈው መንግሥትን ብልሹ አሰራሮችና የኪራይ ሰብሳቢነት ባህል ይቃወም የነበረ ስለነበረ አሜሪካዊው ሂትለር መሆንን ፈጽሞ አልተቀበለም፡፡

ጀኔራሉ ከሚታመን የፊላዴልፊያ ጋዜጠኛ ጋር በመተባበር፣ በቂ ማስረጃዎችን ካሰባሰቡ በኋላ በመንግሥት ምክር ቤት ለሕዝብና ለመንግሥት ተወካዮች በይፋ የተጠነሰሰውን ሴራ በመዘገብ መፈንቅለ መንግሥቱን አጋለጡ፡፡ በዘገባቸው ላይ ሕገመንግሥቱ ካስቀመጠው ውጬ የሕዝብን ድምጽ በመሻር በኃይል ዲሞክራሲያዊውን መዋቅር በማፍረስ ለተዘጋጀውን የተቀናጀ ኃይል መሪነት መመረጣቸውን ሆኖም የሕዝባዊውን የሩዝቬልት መስተዳድርና ሕገመንግሥቱንም እንደሚያከብሩ አስመስክረው የዜግነት ግዴታቸውን ተወጥተዋል፡፡

ፍራንክሊንም በበኩላቸው ይህ የአለማቀፋዊው የንጉሣዊያን ኃያልነት የመደብ ትግል እንደሆነና ዜጎች በንቃት በመተባበር የራሳቸውን መንግሥት በመምራት አጥብቀው እስከመጨረሻው እንዲታገሉት አሳሰቡ፡፡

በታሪክ ስለተለያዩ ጦርነቶችና ግጭቶች ብዙ ቢባልም ስለ አሜሪካና ብሪታኒያ (እንግሊዝ) ፍልሚያዎች ብዙም አልተወሳም፣ የሰው ልጆችን የወደፊት የሥልጣኔ አቅጣጫ አመላካች የሆነው ድርድር በሁለቱ ሥርዓት የበላይ መሪዎች በፕሬዝደንት ፍራንክሊን ሩዝቬልትና በብሪታኒያው ውጭ ጉዳይ ሚ/ር ዊንስተን ቸርችል ውይይት የሩዝቬልት ልጅ ኤልየት ሩዝቬልት የዘገቡት እንዲህ ይገለፃል፤

**ኤልየት ሩዝቬልት-** "ቸርችል በገበታው ተቀምጠዋል ከልሎችም ጋር እየተነጋገሩ ነው፣ እንሂድ?"

**ፍራነክሊን ሩዝቬልት-** "ባለፈው ዊንስተን የተረዳኝ አይመስለኝም፣ በአፍሪቃ ሰማይ ላይ የአየር በረራ ካደረኩ በኋላ ስለ መላው ዓለም ሃገራት የወደፊት ፈንታ የተለየ ግንዛቤ ኖረኝ፣የደቡብ ቱኒዚያን ሰፊ ለጥ ያለ የጨው በረሃ ስትመለከት በአንድ ወቅት በየብስ ውስጥ የነበረ የባህር ወለል እንደነበረ ትረዳለህ፣ ከአትላስ ተራሮች መንጭተው በሳሃራ በረሃ ከርስ የሚሰርጉት የሚቀሩት ወንዞች፣ ተቆፍረው ቢወጡ ያንን በረሃ በመስኖ እርሻ ቢለማ፣ የካሊፎርኒያን ግብርና ያኮስሰው ነበር፡፡ የጨዉ መሬት ቀድሞ እንደነበረው ውኃውን መልሰው በከትሩበት 150 ማየል ስፋት ያለው ባህር መሆን ይችላል፡፡ ይህም እውነተኛ ሃብት ነው፡ ኢምፔሪያሊስቶች በእርግጥ ሃብት ምን እንደሆና እንዴትም ሃብትን መገንባት እንደሚቻል አይረዱም፡፡ እነዚህን ሕዝቦች በቅኝ የዘረፏቸው በረጅሙ ማየት ስላልቻሉ ነው፡ የሰረቁት ቢሊዮኖች ሊሰራ ከሚችለው ጋር ሲነጻጸር የሳንቲም ያህል ነው፡ ይህም ሊሰራ የሚችለው እምቅ የሃብት ክምችት ነዋሪዎቹን በመጀመሪያ ተጠቃሚ ማድረግ ይኖርበታል፡"

ወዲያውኑም ም/ፕሬዝደንት ሄንሪ ዋለስ መጡ እንዲህም አሉ፣

**ም/ፕሬዝደንት ዋለስ** "አንድ ሰዓት ሙሉ ከቸርችል ጋር ተጻረቅሁ፣ ከጦርነቱ በኋላ ብሪታኒያና አሜሪካ በጋራ ኮሚኒዝምን መዋጋት አለብን ሲለኝ፣ ፋሺዝም ኮሚኒዝም ካፒታሊዝም፣ሁሉም ከአንድ አይነት ምንጭና አመለካከት የሚመጡ ናቸው የብሪታኒያም የምጣኔ ሀብት ሥርዓት የተለየ አይደለም አልኩት፣ ዝም ብሎ ጣራ ጣራ በመመልከት ስለ ዳርዊን የቀባጥር ጀመር፤ምን ጅል ነው"

**ፍራነክሊን ሩዝቬልት-** "ሄንሪ ሄንሪ ተረጋጋ፣እነዚህ ሰዎች እኮ የራሳቸው የፈጠሩት ሥርዓት ሰለባዎች ናቸው፣ ሥርዓቱን ከሚጠቀሙበት ይልቅ እነርሱን ይጠቀምባቸዋል፣ እጅጉን ትዕግስተኞች መሆን ይገባናል፣"

**ም/ፕሬዝደንት ዋለስ** "ፍራንክሊን የራሳችን ፋሽስት እዚሁ አገራችን ውስጥ ሥርዓታችንን ለመቀልበስ በማድፈጥ ላይነው፣ ቶሎ ተንቀሳቅሰን መፍትሄ ማምጣት አለብን"

**ፍራነክሊን ሩዝቬልት-** "እውነት ነው፣ ግን ከጦርነቱ በኋላ ይህ ትብብር አስፈላጊ አይሆንም፡፡ ይህን ጦርነት በድል ከተወጣን በኋላ፣ ባለኝ ሁሉ ጉልበት አሜሪካ የፈረንሳይ ኢምፔሪያሊዝምንም ሆነ የብሪታኒያ የኢምፔሪያሊዝምን አመለካከት በራሷ ላይ ለሸከም እንደማትፈቅድ ቃል እገባልሃለሁ"

ኤልየት ሩዝቬልት፣ ዋለስና ፍራንክሊን ወደ ግብዣው ገቡ፡ ከቸርችልና ከተቀሩት ተጋባገች ጋር በሉ ጠጡም፡ ቀጥሎም ፕሬዝደንቱ ከፍ ባለ ድምጽ፣ ቸርችል እንዲሰሙ አድርገው ለሌላ ተጋባዥ ይህን አሉ

**ፍራነክሊን ሩዝቬልት-** "ይገርምሃል ሚኒስቴሩ ሕዝባችን ስለ ብሪታኒያና ስለምታራምደው አቋም ምን ያህል እንደተማረረ ሊገባቸው አልቻለም፣ ይህ የሕዝብ ጥርጣሬ እንዲሁም ጥላቻ በአሜሪካ ኅብረተሰብ ልብ ውስጥ ሰርጿል፣ እርግጥ ብዙ አይነት አሜሪካውያን አሉ፣ ነገር ግን እንደ ሕዝብና እንደ ሃገር ኢምፔሪያሊዝምን እንጠላለን፡ ተፈጥሯችንም አይቀበለውም" ብለውም በፈገግታ ቸርችልን ተመለከቷቸው፣ ሚ/ሩም ዝም ብለው የጨው አምድ መስለው ተቀመጡ፣ቀጥለውም "ዋናው ነጥብ ብዙ አሜሪካዊያን ፀረ-ብሪታኒያ ናቸው፣ለምሳሌ እኔ ዛሬ የብሪታኒያ ጠላት አይደለሁም ግን በልጅነቴ እናቴ ወደ እንግሊዝ ወስዳኝ ስነበኝ ንግሥት ቪክቶሪያ በሠረገላዋ ስትጓዝ ተመልክቻት ከባድ ጥላቻ አደረብኝ"

በዚያን ወቅት ተጋባገች ቀስ በቀስ ለቀው ሄዱ፣ በመጨረሻም አራታችን ብቻ ቀረን፣ ቀጥሎም ፖለቲካና ስለ ድህረ ጦርነት ምጣኔያዊ እቅድና መርሃ ግብር ይወያዩ ጀመር፡

**ፍራነክሊን ሩዝቬልት-** "የንጉሣዊው የንግድ ስምምነቶች በሙሉ መሻር ይኖርባቸዋል፣ ለዚህም ነው ህንድ፣አፍሪቃ፣ በቅኝ የነበሩት ቅርብና ሩቅ ምስራቅና በሙሉ ድሃና ኋላቀር የሆኑት፡"

**ዊንስተን ቸርችል-** "ፕሬዝደንት ሩዝቬልት፣ ብሪታኒያ የምትቆጣጠራቸውን ግዛቶች ለመልቀቅ ከማንም ጋር አትደራደርም፣ ብሪታኒያን ታላቅ ያደረጓት አወቃቀሮች ባሉበት ይቀጥላሉ፣ ለውጥም ካሰብን በሚኒስቴሮቻችን ምክር ብቻ ነው ሊሆን የሚችለው"

**ፍራነክሊን ሩዝቬልት-** "የአሌክሳንደር ሃሚልተን ዘገባ የኛ የአሜሪካን ሥርዓት መርህ በልማታዊ መንገድ ብዙሃኑን የሚጠቅምና ፈጣን የምጣኔ ሃብት እድገትን ያመጣ እንደሆነ ያሳያል፡ ሁልጊዜም

የሚሰራ መርህ ነው፡ በዚህ መርህም ቻይናን በኢንዱስትሪ ልማት ለማገዝ ንድፍ አውጥቻለሁ፣ ነገም ይተገበራል፡፡”

**ዊንስተን ቸርችል-** “ምን ዓይነት ስህተት እየሰራህ እንደሆነ ላስጠነቅቅህ ፈልጋለሁ፡”

**ፍራንክሊን ሩዝቬልት-** “አለምአቀፍ ሰላምና መረጋጋት ላይ ለመድረስ ከፈለግን የኋላቀር ሃገሮችና ኋላቀር ሕዝቦች መሻሻል አማራጭ የሌለው ጉዳይ መሆኑ ላይ ጥልቅ እምነት አለኝ፡ ይህ ደግሞ በ18ኛው መቶ ክፍለ ዘመን አሰራር ሊተገበር አይችልም”

**ዊንስተን ቸርችል-** “ማን ነው ስለ 18ኛ ዘመን አሰራር የሚያወራው”

**ፍራንክሊን ሩዝቬልት-** “ማናቸውም የናንተ ሚኒስቴሮች የሚመክሩት የ18ኛ ዘመን ሥርዓት የሃገራትን የተፈጥሮ ሃብትና ጥሬ ማዕድናት ያለተመጣጣኝ ክፍያ በመውሰድ ሲሆን፣ የ20ኛ ዘመን አሰራር ደግሞ ኢንዱስትሪን ወደነዚህ አገሮች በማስገባት የጥቅሙም ተቋዳሽ ማድረግ ነው፡ የ20ኛው ዘመን አስተሳሰብ የሕዝቦችን ሃብት ማሳደግ፣የኑሮ ደረጃቸውን ማሳደግ፣ በትምህርት፣ ጽዳትን በማምጣት እንዲሁም ለጥሬ ሃብታቸው ትክክለኛውን ዋጋ መክፈል ነው፡፡ ሕንድን ተመልከት የፋሽስትን ባርነትን እየተዋጋን የአለምን ነፃ ሕዝቦች ከኋላቀርነትና ድህነት አረንቋ ለማውጣት አንፈልግም”

**ዊንስተን ቸርችል-** “የብሪታኒያ ሥርዓት መዋቅርን መነካካት አይፈቀድም”

**ፍራንክሊን ሩዝቬልት-** “ዘላቂነት ግን የለውም፣ ቀጣይም አይደለም”

**ዊንስተን ቸርችል-** “መሠረታዊ ናቸው... በእኔ እምነት እርስዎ የብሪታኒያን ሥርዓት ለማፍረስ ነው የተነሱት፣ የሚያፈልቋቸው ሃሳቦች በሙሉ ይህንን ነው የሚያመላክተው፣ ግን ቢሆንም...፣ ቢሆንም ያለአሜሪካ እገዛ ተስፋ እንደሌለን እርስዎም ያውቃሉ፣ እኛም የዘውድ ሥርዓታችን ብቻውን ያለናንተ ትብብር መቆም እንደማይችል እናውቃለን”

ብለው የግዴታ ፈገግታ አሳይተው ምሽቱን ፈጸሙ ወደ መኝታቸውም አመሩ፡፡

**ፍራንክሊን ሩዝቬልት-** ድምጻቸውን ዝቅ አድርገው ለልጃቸው እንዲህ አሉ “ምርጫው የኛ ነው፣ያለንን ጠንካራ ተጽዕኖ የመፍጠር አቅማችንን ተጠቅመን መላውን ኃያላንን ወደኅብረት ማምጣት ይቻለናል፣ ሃገራችን ታሪካዊ ኃላፊነት አለባት”

የሩዝቬልት አላማም፣ከጦርነቱ ፍጻሜ በኋላ የነበሩት ኃያላኑ አራት መንግሥታት ማለትም አሜሪካ፣ ብሪታኒያ፣ ቻይናና፣ የሶቪየት ኅብረት ኃላፊነቱን ወስደው የንጉሣዊው የአንድ የዓለም መንግሥትን ሃሳብ (The New World Order) በማፍረስ የተለያዩ ብዙሃን ሉዐላዊ መንግሥታትን ሕብረት በማቋቋም የተባበሩት ማንግሥትን መመሥረት ነበር፡፡ ይህም ኅብረት በአትላንቲክ ስምምነት መርህ ስር ከኃላፊነቱ መካከል ቅኝ አገዛዝ ከምድር ማስወገድና፣ የትክኖሎጂ ልማት ኃይልን ለአለም ሁሉ ማሰራጨት ቀዳሚዎቹ ነበሩ፡፡

በሩዝቬልት መሪነት ለአለማቀፋዊ ትብብሮችን ምቹ ሁኔታዎችን በመፍጠር አሜሪካ ለአለም የብሩህ ተስፋ ፋና ወጊ ሆና ወጣች፡፡ ይህም ሊንከን ከሞቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የአለም የፀረ-ኢምፔሪያሊዝም ትግል አንሰራርቶ፣ በሕዝባዊ አቅጣጫም የኦሊጋርኪውን ሥርዓት ወደ ማጥፋት

ግብ በመንቀሳቀስ ውጤት ማስመዝገብ ጀመረ፡፡ የተባበሩት መንግሥታትም በራሳቸው የቆሙ የሉዐላዊ መንግሥታት በማሰባሰብ የተደራጀ የሃገራት ማኅበረ ሰብ ሆነ፡፡

በሩዝቬልት በተመረጡትና በትረመንግሥቱን ቀጥለው ለመረከብ ተሰናድተው እንደነበሩት እንደምክትል ፕሬዝደንት ሄንሪ ዋለስ አካሄድ ቢሆን በነሊንከን የተጀመረው ሕዝባዊ ትግል በተሳካ ነበር፡፡ በንግግራቸው *“አንዳንዶች ያለንበትን ጊዜ የአሜሪካ ወርቃማ ሰዓት ይሉታል፣እኔ ግን ከልባችን ለሰው ልጆች ሰላም የምንታገል ከሆነ የጀመርነው ክፍለ ዘመን ከጦርነት የምንወጣንበት ዘመን፣ የመላው ዓለም ሕዝቦች ሁሉ ዘመን ነውም መሆንም አለበት እላለሁ፡፡ ትግሉ በባርነትና በነፃነት መካከል ነው፡ ልክ በ1862 አሜሪካ በከፊል ነፃ ከፊል ባሪያ ሆኖ ሊቀጥል እንዳልተቻለው፣ የተቀረውም ዓለም በ1942 ከሁለቱ አንደኛው ወገን አይሎ ሙሉ ድልን ማግኘት ይኖርበታል፡፡ ሕዝቦች በያዙት የለውጥና ለመብታቸው በመዋደቅ ባሳዩት ትግል፣ ስብዕና ያለው ሁሉ በ1941 ፕሬዝደንት ሩዝቬልት ያስቀመጡትን ባለ አራት ነጥብ የነፃነት ገጽታዎች የሚሻ እንደሆነ ሊሰመርበት ይገባል፡፡*

*በዛሬዋ ነፃ አሜሪካ የምንኖር ግን የእምነትና የመናገር መብት ለማስከበር፣ ከስለላና ከስውር አምባገነናዊ ኃይሎች ነፃ የሆነ ሕይወትን ለመምራት ለሚደረግ ትግል ብዙም ዋጋ ላንሰጠው ብንችልም፣ ነገር ግን የሰው ልጆች መሠረታዊ ፍላጎቶች (ምግብ፣ልብስ፣መኖሪያ) አለመሟላትን ስናስብ እዚሁ አገራችን ውስጥም ሆነ በዓለም ዙሪያ ከ150 ዓመታት በፊት የተጀመረው አብዮት ገና ግቡን ለመምታት ብዙ እንደሚቀረው እናያለን፣ እነዚህ ፍላጎቶች እስካልተሟሉ ድረስ ትግሉ መቋረጥ የለበትም ”፡፡*

በሚያሳዝን ሂደት የሩዝቬልት ጤና በመስተጓጐሉም፣ ጦርነቱም ወደማለቂያው ስለነበረ፣ በዴሞክራቲክ ፓርቲ የውስጥ የብሪታኒያ ጥቅም አስጠባቂዎች ፕሬዝደንቱ ላይ ተጽእኖ በማድረግ ምክትላቸውን ዋለስን በሄንሪ ትሩማን እንዲቀይሩ አደረጉ፡፡ ለቀጣዩ የ1944ቱ ምርጫ ትሩማንን ሲያዘጋጁ፣ በአቋሙ የሩዝቬልትን አስተምሮት የተከተለ ሳይሆን የዊንስተን ቸርችልን የድህረ ጦርነት እይታን የተቀበለ ነበር፡፡ ሩዝቬልት ሲሞቱ ወዲያው ብዙ ሃገራት ልዕልናቸውን ለማረጋገጥ እየተቃረቡ ሳሉ ብሪታኒያና ደች ተመልሰው ወደ አፍሪቃ፣ ቻይና፣ ኢንዶኔዢያና ሌሎችም ሃገራት ተመልሰው በመግባት ቅኝን በድጋሚ አጠናክረው ቀጠሉ፡

ጃፓን እጅ ለመስጠት ድርድር ጀምራ ሳለች ሄሪ ተሩማን ሀለት የኑክሌር ፈንጂዎች ጣሉባት፣ በሰላማዊ ትብብር በአለም ዙሪያ የመልሶ ግንባታ ዘመቻ ከማካሄድ ይልቅ አሜሪካ ከብሪታኒያ ጋር በመወገንና ከሶቪዬት ኅብረት ጋር በመፋጠጥ ለሚቀጥሉት 40 ዓመታት መላው ዓለም በሁለት ጎራ እንዲከፈል አደረጉ፡፡ ከጥቂቶች በስተቀር የአሜሪካ መስተዳድር የብሪታኒያን የነፃ ገበያ አሰራርና መልሶ እንዲያንሰራራና በአለም ምጣኔ ሃብታው ግንኙነት የራሱን ዘላለማዊ የሚመስለውን የበላይነት ማዝለቅ የሚያስችለው መስመር ያዘ፡፡

ሥርዓቱን ለመቃወም ወይም ለመቀየር የሞከሩ እንደ ጆን ኤፍ ኬኔዲ፣ ማልከም ኤክስ፣ ማርቲን ሉተር ኪንግ፣ሮበርት ኬኔዲ አይነት መሪዎች ተገደሉ፡፡ ፍራንክሊን አስቦትና ወጥኖት የነበረው የድህረ ጦርነት አቅጣጫ ዛሬም በንድፈ ሃሳብነት ቁጭ ብሎ ያስፈፃሚ ያለህ በማለት ይጣራል፡፡

ሊንከን በነዚሁ ብሪታኒያዎች ሲገደሉ፣ ሕዝብና ተከታዮቻቸው በቁጭት ትግሉን አፋፉሙት፤ ሩዝቬልት ግን በራሱ ሞተ፣ ስለዚህ ብዙም ቁጭት ሳየቀሰቅስ አለፈ፡፡ በሌላ እይታ ብንመለከተው፣የሁለቱና መሰል  መሪዎችን ልዩ አስተሳሰቦች ብናራምድ፣ የአእምሮ ውጤታቸውን፣

ሃሳቦችን የማፍለቅ የማሰራጨትና የመተግበር ችሎታቸውን፣ የፈጠራ ችሎታቸውንና ሌሎችን የማደራጀትና የሌሎችን አቅም የመገንባት ችሎታቸውን፣ በአጠቃላይ ለጠንካራ መሪዎች መልካም አስተሳሰብ የሚገባውን ዋጋ ብንሰጥ፣ ልክ ሩዝቬልት እንደተረዳው "ሰው በአስተሳሰቡና ባህሪው እንጂ የአካሉ የተሟላ ደህንነት ከፍተኛው ነገር እንዳልነበረ"፣ እነደነዚህ የሠማዕት ጓዶቻችንንና መሪዎቻችንን አስተምሮቶች ካዳበርንና በቁርጠኝነት ከቀጠልንባቸው ኅልፈታቸው ያን ያህል ማንነታቸውንና ታሪካቸውን አያሳንሳቸውም፡፡ በእኛ ውስጥ የበለጠ ሕያው ይሆናሉ፡፡

የግለሰቦች የአመራር ብቃት እንጂ የሁኔታዎች መከሰት አይደለም የዓለምን የታሪክ አቅጣጫ የሚወስነው፣ በብሪታኒያ የተመሠረተውን የጥቂቶች ፀረ-ብዙሃን ኢ-ፍትሐዊ የነፃ ገበያ አስተሳሰብ በሕዝባዊና ጠንካራ ልማታዊ አስተሳሰብ የሰውን ልጆች አለማቀፋዊ ያለስጋት የመኖርን ተፈጥሮዋዊ መብትን በተባበረ በትግላችን እናረጋግጥ፡፡

ወንድወሰን ታደሰ

ኦክላንድ  አሜሪካ